የተጠቃሚ ስም፤ ___________________________
የአያት ስም፣ የመጀመሪያ ስም (ይጻፉ)
ክፍል/የሥራ ድርሻ፤ ___________________________

Training Date/Class:____________
(የስልጠና ቀን/ክፍል)

For School/District use only.
(ለትምህርት ቤት/ድስትሪክት ሥራ ብቻ።)

**የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት**
**የተገናኙ መስመሮች(ድረ ገጽ) አገልግሎቶች የመጠቀም ስምምነት**
**የተጠቃሚዎች/የወላጆች/የአሳዳጊዎች የስምምነት ቅጽ**

**ጠቅላላ መረጃ**

ተማሪዎች እና ሰራተኞች በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት የተገናኙ የታገዙ መረጃዎችን በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ማግኘት ይችላሉ። የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ሰፊ የሆነ ድረ ገጽ እና ሁሉንም የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች የሚያገናኝ እና ኢንቴርኔትን ጨምሮ፣ በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ሥርዓት የተገናኙ የመረጃ ምንጮችን የሚሰጥ ነው። ኢንቴርኔት ውስብስብ በሆኑ የመንግሥት ድርጅቶች/ተቋማት እና በተገናኙ የመረጃ መስመሮች የሚቀናበር ሲሆን፣ እንደ የኤሌክትሮኒክስ ቀለበት መንገድ ሆኖ በሺዎች የሚቆጠሩትን ኮምፒዩተሮች የሚያገናኝ እና ከመላው ዓለም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን የኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች የሚያገናኝ የመረጃ ምንጭ ነው። የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ብዙ የትምህርት የመረጃ ምንጮችን ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ይሰጣል። ይህንን የመረጃ አገልግሎት የመስጠት ዓላማው በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ያሉትን መረጃዎች ለመስጠት፣ ለማሻሻል እና መረጃ በመለዋወጥ ምርጥ የሆነ ትምህርት ለመስጠት እና የተማሪ የትምህርት ክንውንን ለማሻሻል ነው።

የተገናኙ የመረጃ መስመሮችን እና ሥርዓቶችን ያለችግር መጠቀም የሚቻለው የተጠቃሚዎች ጥብቅ የሆኑ መመሪያዎችን የማክበር እና የመከተል አግባብ ያላቸው ምግባራት ላይ ይሞረኮዛል። የተጠቃሚዎችን ኃላፊነት የሚገልጹ መሰረታዊ የሆኑ መመሪያዎች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል። ተጠቃሚዎች ከተሰጡት መመሪያዎች ውስጥ አንዱን ቢጥሱ፣ የተጠቃሚው/ዋ የኮምፒዩተር አካውንት/ፋይል ይዘጋል፤ ለወደፊትም ኮምፒዩተሩን መጠቀም ሊከለከል/ሊትከለከል ይችላል/ትችላለች። የቅጣት እርምጃም ሊወሰድ ይችላል። የወንጀል ድርጊት ከተገኘ፣ ጉዳይ አግባብ ላላቸው ባለ ሥልጣናት ይገለጻል። ለተማሪዎች የሚሰጠው የቅጣት እርምጃ ባሉት የስነ ምግባር ፖሊሲዎች ሲሆን፣ ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ እና/ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላከን ሊያካትት ይችላል። በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ የሰፈረው ፊርማ ወገኖቹ ሁኔታውን በደንብ አንብበው የገባቸውና ጉዳዩን የተቀበሉት መሆኑን ያረጋግጣል።

**የተጠቃሚ መመሪያዎች**

1. የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ መጠቀም በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ዓላማዎች ጋር በሚስማማ መልኩ መሆን አለበት። የፌዴራል ወይም የክፍለ ግዛት ህግን ወይም የመተዳደሪያ ደንብን በሚጥስ ሁኔታ ማንኛውንም ዓይነት መረጃ ማሰራጨት ክልክል ነው። ከቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት አስቀድሞ የጽሁፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ለንግድ ተግባራት መጠቀም ክልክል ነው።

2. የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የመረጃ ሥርዓቱ የተወሰኑ መስፈርቶችን እንደሚያሟሉ ወይም ስሕተት ወይም ችግር እንደለለባቸው አያረጋግጥም ወይም ዋስትና አይወስድም፤ እንደዚሁም ለማንኛውም ቀጠኛም ሆነ ቀጥተኛ ላልሆነ፣ ለአጋጣሚ ክስተቶች፣ ወይም ለሚፈጠሩ ችግሮች/ጉዳቶች (የመረጃ መጥፋትን ጨምሮ) በዘላቂነትም ሆነ ለጊዜው የመረጃ ሥርዓቱን መጠቀም አለመቻል አስመልክቶ ድስትሪክቱ ዋስትና አይወስድም።

3. ኢንተርኔትን የሚጠቀሙ ሁሉንም ተማሪዎች መቆጣጠር እንደማይቻል ግልጽ ነው። ነገር ግን፣ በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት መሰረት የድስትሪክቱን ድረ ገጽ የአጠቃቀም ሥርዓቶችን ሳይከተሉ አግባብ በለላቸው መንገዶች መጠቀም፣ ወይም አግባብ በለለው መንገድ ሌሎች የድስትሪክቱ ድረ ገጽ እንዳይጠቀሙ ማገድ/መከልከል በፍጹም የተከለከለ እና የተጠቃሚዎችን የመረጃ ሥርዓቱን የመጠቀም ልዩ መብት ሊያከለክል ይችላል፤ እንደዚሁም የቅጣት እርምጃም ሊያስከትል ይችላል። ማንኛቸውንም የሰውን ስም የሚያጠፉ፣ ትክክል ያልሆኑ፣ ግፍ የሆኑ፣ መጥፎ፣ ወሲብ ነክ፣ ዛቻ ያለበት፣ ጎሳን የሚያስቆጣ ወይም ሕገ ወጥ የሆነ ጽሁፍን በቼሪ

ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ማግኘት፣ በድረ ገጹ ላይ ማስገባት፣ ማሳተም፣ ወይም ማሳየት እንደማይቻል ተጠቃሚው/ዋ በግልጽ ይስማማል/ትስማማለች። በተጨማሪም፣ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽን በቅጅ መብት ሕጎች መሰረት መጠቀም እንዳለበት/እንዳለባት ተጠቃሚው/ዋ ይስማማል/ትስማማለች። የቅጅ መብት ያላቸውን ጽሁፎች መቅዳት፣ እንደ የግል አድርጎ መያዝ ወይም ማሰራጨት አይፈቀድም፤ ተጠቃሚዎችም፣ በይፋ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ጽሁፎች የቅጅ መብት እንዳላቸው መገመት አለባቸው።

4. የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የኢንቴርኔት ይዘቶችን እና ኢንቴርኔት መጠቀምን አይቆጣጠርም፣ ሊቆጣጠርም አይችልም። ስለዚህም ተጠቃሚዎች ከኢንቴርኔት ለሚያገኙት መረጃዎች እና ከጎጂ/መጥፎ መረጃዎቹ የተነሳ በሚደርስባቸው ጎጂ የሆኑ ተጽኖዎች ድስትሪክቱ ኃላፊነት አይወስድም። ማንኛውንም መረጃ በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ መጠቀም የተጠቃሚው/ዋ ኃላፊነት ነው። የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት በድረ ገጹ ለሚገኙት የመረጃዎች ትክክለኛነት ወይም ጥራት ኃላፊነት አይወስድም፣ በተጨማሪም በመረጃ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉትን የመረጃዎች ይዘት አይቆጣጠርም። ምርቶች እና አገልግሎቶች በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ላይገዙ ይችላሉ። በድስትሪክት ኮምፒዩተሮች ውስጥ የተከማቹ ፋይሎች፣ ኢሜል እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ጥቅም ለግል አይደሉም፣ እናም ፍተሻ እና/ወይም ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይችላል።

5. ሆን ብሎ በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች ማጥፋት፣ ማውደም ወይም መረጃዎቹን መለወጥ የመረጃ ሥርዓቱን የመጠቀም መብት ያስከለክላል። ክልክል የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት መሞከር የመረጃ ሥርዓቱን የመጠቀም መብት ሊያስከለክል ይችላል፤ የቅጣት እርምጃም ሊያስከትል ይችላል። የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ አስተዳደሮች ማንኛውንም ወይም ሁሉንም የመረጃ ሥርዓት የመቆጣጠር መብት አላቸው።

እኔ/እኛ ከላይ የተሰጡትን ቅድሚ ሁኔታዎችን መቀበለን/መቀበላችንን እና መስማማተን/መስማማታችንን፣ እንደዚሁም ለልጄ ወይም በሃላፊነት ለማስተዳድረው/ለማስተዳድራት ልጅ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ድረ ገጽ እንዲጠቀም/እንዲትጠቀም እፈቅዳለሁ።

______________________________ ______________________________

የተጠቃሚ ስም ትምህርት ቤት ወይም ቦታ

______________________________ ______________________________

የተጠቃሚ ፊርማ ቀን

______________________________ ______________________________

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ(ተጠቃሚ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ/ች) ቀን